# ልዑል እግዚአብሔር፥

## እንኳን፥ ለ፳፻፲፫ኛው (ለሃያ መቶ [ኹለት ሺ] ሦስተኛው)
## ጾመ ፍልሰታ ለማርያም እና ጾመ ጳጒሜ፥
## በያለንበት፥ በደኅና አድርሶ፥ ሱባኤያችንን ለመጀመር አበቃን!

እኛ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ በዓመቱ ውስጥ ከምንጾማቸው፡ ከሰባቱ አጽዋማታችን መካከል፡ ፪ተኛዋ፡ "ጾመ ፍልሰታ" ናት፡፡ እርሷንም፡ ለኹለት ሳምንታት በሚዘልቅ ሱባኤ፥ ከነሓሴ ፩ እስከ ፲፭ ቀን ድረስ እንጾማታለን ፡፡

"ፍልሰታ"፡ "ፈለሰ" ከሚለው የግእዝ ቃል የወጣ ሲኾን፥ እርሱም፥ "አንድ ሰው፡ ካለበት ቦታ ተነሥቶ፥ ወይም፡ ነቅሎ፡ ወደሌላ ተዛወረ!" የሚል ትርጒም ያለው ነው፡፡ ይህ ቃል፥ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ መዋል የሚጀምረው፥ የመለኮትና የትስብእት ተዋሕዶ ተፈጽሞበት፡ እግዚአብሔር ወልድን ፀንሶ የወለደውና አጥብቶ ያሳደገው፡ የቅድስት ድንግል ማርያም፡ አካለ ሥጋዋ፡ ከነፍሷ ከተለየበትና አይሁድ እርሱን በእሳት ሊያቃጥሉ በመሞከራቸው፥ በመላእክት ተነጥቆ፥ ወደገነት ከተወሰደበት፥ ከዕረፍቷ ዕለት፥ ከጥር ፳፩ ቀን አንሥቶ ነው፤ ተያይዞም፥ የሓዋርያት የኹለት ሳምንት ሱባኤ፥ ፍሬያማውን ምላሽ በማግኘቱ፥ በነሓሴ ፲፬ ቀን፥ ከገነት ወደምድር ተመልሶ ከተቀበረና፥ ከነፍሷ ጋር ከተዋሓደ በኋላ፥ በነሓሴ ፲፮ ቀን፥ እንደልጇ፥ በሦስተኛው መዓልትና ሌሊት፡ ከመቃብር የመነሣቷን፥ በአርባኛውም ዕለት፥ በመስከረም ፳፩ ቀን፥ እንደኢየሱስ ክርስቶስ፡ ወደሰማይ የማረጓን ነገር አክካትቶ ለማዘከር ተብሎ የተመደበ ቃል ነው፡፡

ቸሩ ፈጣሪያችን፡ ይህን ከመሰለው ጾም ጸሎታችንና ሱባኤያችን የተነሣ፡ በያለንበት፡ በሕይወትና በጤንነት አቆይቶን፡ ከዚሁ ጊዜ ለመድረስ ካበቃን፡ ይህችኑ፡ የዘንድሮዋን፡ የፍልሰታ ጾማችንን፡ እንደተለመደው፡ እያንዳንዳችን፡ እንደየዓቅማችን፡ ስለራሳችንና ስለወገናችን፥ ስለአገራችንም ብቻ ሳይኾን፡ ስለዓለሙ ኹሉ ደኅንነት ጭምር፡ በእውነተኛ ንስሓ ተመልሰንና በሱባኤ ተጠምደን፡ በምናካኺደው የምሕላ ጸሎታችን፡ ልንፈጽማት ይገባናል፡፡ ይኸው ጾማችንና ጸሎታችን፥ ምሕላችንና ሱባኤያችን፡ ከዚህ በፊት፡ ለ"ጾመ ኢትዮጵያ" ተዘጋጅቶልን የተገለገልንበትን፡ ያንኑ ሥርዓትና መመሪያ የተከተለ ይኾናል፡፡ ይህንም፡ የ"ጾመ ኢትዮጵያ"ን፡ የጾምና የጸሎት፥ የምሕላና የሱባኤ ሥርዓትና መመሪያ፡ በዚሁ የጎዋ ሰሌዳ ላይ፡ "ቤተ መዛግብት" በሚለው ክፍል ውስጥ እናገኘዋለንና፡ ያን ከፍተን፡ በመመልከት፥ ዐትመንም በማውጣት፡ ልንጠቀምበት ይቻለናል፡፡

ይህች የጾመ ፍልሰታ ሱባኤ፡ በኢትዮጵያ ምድር ለምንኖረው፡ በዝናቡ የክረምት ወራት ከሚፈጸሙትና ትዝ ከሚሉን ባህሎቻችን መካከል፡ ቀዳሚዋና ዋናዋ ኾና ትገኛለች፡፡ በእርሷም፡ ካህናት፥ ትላልቆች ወንዶችና ሴቶች ምእመናን፥ ብላቴኖችና ልጆች ብቻ ሳይኾኑ፡ ሕፃናት ጭምር እየጾሙ፥ እያስቀደሱና እየቆረቡ፡ የኹለት ሳምንት የሱባዔ ጊዜያቸውን፡ በቤተ ክርስቲያንና በየቤታቸው ያሳልፋሉ፡፡

በጾመ ፍልሰታ ሰሞን፡ የሃይማኖታችንና የአገራችን፥ የእናታችንና የንግሥታችን፡ የቅድስት ድንግል ማርያም፡ ዜና ልደቷ፥ ሕይወቷና ዕረፍቷ፥ እንዲሁም፡ እግዚአብሔር፡ እርሷን ምክንያት አድርጎ፡ ራሱን፡ ለፍጥረቱ የገለጸበትንና ፍጥረቱን ያዳነበት፡ የሥጋዌው፡ ማለትም፡ ሰው የኾነበት ምሥጢር ተብራርቶ ይነገርበታል፡፡ ቅዱሳን ሐዋርያት፡ ይህን ሱባኤ፡ ለምን እንደጀመሩት፥ በዓመቱም እንዴት እንደቀጠሉት፡ ዜና መዋዕሉ ይውወስሳል።

በዚያን ዜና መዋዕል ውስጥ፡ ተካትተው ከሚቀርቡት፡ ዋና ዋናዎቹ ድርጊቶች መካከል፡ ፩ኛ፡ በጥር ፳፩ ቀን ከኾነው ከድንግል ማርያም የሥጋ ዕረፍት በኋላ፡ አይሁድ፡ በተለመደ ጠላትነታቸው፡ አስከሬኗን፡ "እናቃጥላለን !" ማለታቸው፥

፪ኛ፡ በዚያን ጊዜ ግን፡ እግዚአብሔር ወልድ ሰው ኾኖ የተፀነሰበት፥ እስኪወለድ የኖረበትና ጠብቶ፡ በእቅፏ ያደገበት መቅደስ ሥጋዋ፡ በቅዱሳን መላእክት ተነጥቆ፡ ወደገነት መፍለሱ፥ መወሰዱ፥

፫ኛ፡ ወንጌላዊው ዮሐንስ፡ ይህንኑ ምሥጢር ያየ ሲኾን፡ ሌሎቹ ሐዋርያት ባለማየታቸው፡ በነሐሴ ፩ ቀን ሱባኤ መግባታቸውና ምሥጢሩ ተገልጦላቸው፡ እንደገና፡ ወደምድር የፈለሰ ቅዱስ ሥጋዋን ተቀብለው፡ በነሐሴ ፲፬ ቀን፡ በዕለተ እሑድ መቅበራቸው፥

፬ኛ፡ በሦስተኛውም ቀን፡ ለማግሰኞ አጥቢያ፡ እኩለ ሌሊት ላይ፡ እንደልጇ፡ ከሙታን ተለይታ መነሣቷና በ፵ኛው ቀን ማረጓ፥

፭ኛ፡ ይህንኑ ትንሣኤዋንና ዕርገትዋን ለማየትና ምስክር ለመኾን የታደለው፡ ቀድሞ፡ የልጇን ትንሣኤ፡ የመጀመሪያ ምሥራች፡ ከቀሩት ሐዋርያት ጋር ለመስማትና ለማየት ሳይታደል ቀርቶ የነበረው፡ ለጊዜው ሐዋርያው ቶማስ ብቻ መኾኑ፥

፮ኛ፡ ልጇ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ለትንሣኤና ለዕርገት፡ በኵር፡ ማለትም፡ ቀዳማዊው ኾኖ፡ እርሷ፡ ድንግል ማርያም ደግሞ፡ ለዚያ፡ ለትንሣኤውና ለዕርገቱ ብኵርና፡ ዳግማዊትነትና ተከታይነት የበቃችበትን፡ ይህን የመለኮት ድንቅ ኃይል፡ በዚህ ጊዜ ለማየት ከመካከላቸው፡ የታደለው፡ ሐዋርያው ቶማስ ብቻ ስለነበረ፡ "እርሱ፡ ትንሣኤሽንና ዕርገትሽን አይቶ፡ እኛ፡ ለዚህ ዕድል፡ እንዴት ሳንበቃ ቀረን?" በማለት፡ የቀሩት ሐዋርያት አዝነው፡ በዓመቱ፡ በነሐሴ ፩ ቀን፡ ለኹለተኛ ጊዜ ሱባኤ መግባታቸው፥

፯ኛ፡ በመጨረሻ፡ ነሐሴ ፲፮ ቀን በሚውለው በትንሣኤዋ መታሰቢያ ዕለት፡ ሐዋርያት፡ ወደሰማያዊቷ የእግዚአብሔር መንግሥት ተነጥቀው ኼደው፡ ቅድስት ድንግል ማርያም የምትገኝበትን ክብርና ምስጋና ማየታቸው፥ ልጇ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ እርሷን፡ እናቱን፡ መንበር፥ ራሱን፡ ሠራዒ ቄስ፥ ሊቀ ሐዋርያት ጴጥሮስን፡ ረዳት ካህን፥ ቀዳሜ ሰማዕት እስጢፋኖስን፡ ሠራዒ ዲያቆን አድርጎ፡ ቀድሶ፡ እነርሱን ማቍረቡ፡ በአርእስት ተከፋፍሎና በዝርዝር ተተንትኖ ይነገራል፡፡

# በዓለ ፍልሰታ ለማርያም፡-
# ሰማያዊ ልዕልናው፡፡

“ትንሣኤሃ ለማርያም” በሚል ስያሜ፡ ነሓሴ ፲፮ ቀን ስለምትከበረው፡ የቅድስት ድንግል ማርያም፡ የትንሣኤዋና የዕርገትዋ መታሰቢያ ስለኾነችው በዓለ ዕለት፡ ለማስረዳት፡ ከዚህ የሚከተለው ሓተታ፡ በጥቂቱም ቢኾን ቀርቧል፡፡

የዘመነ ኦሪቷ ጽላተ ኪዳን ታቦት፡ ምሳሌዋ የኾነችው፡ የእግዚአብሔር ወልድ እናት፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ ለመጨረሻው፥ ለኹለንተናዊውና ለዘለዓለማዊው ትንሣኤና ዕርገት፡ በኵር ከኾነው፡ ከልጇ፡ ከኢየሱስ ክርስቶስ ቀጥላ፡ በአዲስ ኪዳኑ የትንሣኤ አካል፡ ከሙታን ተለይቶ የመነሣትና የማረግ ክብር ያገኘች መኾኗን፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ በሃይማኖት የተቀበሉት እውነታ ነው፡፡

በዚያች ጽላተ ኪዳን ላይ፡ በራሱ፡ በእግዚአብሔር ጣቶች የተጻፈው፡ ራሱ እግዚአብሔር ቃል፡ የተቀረጸባትን ጽላት፡ የራሱ አካል አድርጎ፡ በዘመነ ብሉይ፡ መለኮታዊ ክብሩን እንደገለጸባትና አምላካዊ ኃይሉን እንደፈጸመባት ኹሉ፥ ኋላም፡ በዘመነ ሓዲስ፡ በዚያው ባሕርያዊ ጥበቡ፡ ከሥጋዋ፡ ሥጋን፥ ከነፍሷም፡ ነፍስን ነሥቶ፡ በተዋሓዳት፡ በቅድስት ድንግል ማርያም ሠውሩዋት፡ ያን፡ በትንሣኤውና በዕርገቱ፡ እውንና ገሃድ ያደረገውን፡ አማናዊዉንና ዘለዓለማዊዉን ክብሩንና ኃይሉን፡ ለእርሷም አጐናጽፎ፡ እናቱን፡ ለፍጹሙ ሕያው ማንነቷ አብቅቷታል፡፡

የዚህ እውነታ መነሻ፡ ድንግል ማርያም፡ “**ትፀንሲ!**”፣ ማለትም፡ “**ትፀንሻለሽ!**” ያላትን፡ የመልአኩን የቅዱስ ገብርኤልን የምሥራች ቃል ተቀብላ፡ “**ይኵነኒ በከመ ትቤለኒ!**” ማለትም፡ “**እንዳልኸኝ (እንደቃልህ) ይኹንልኝ!**” ባለችበት ቅጽበት፡ “**ቃል ሥጋ ኾነ!**” ማለትም፡ “**አምላክ ሰው ኾነ!**” በሚለው የሥጋዌ ምሥጢር፡ የተፈጸመው ዕፁብ ድንቅ ተአምር ነው፤ የዚሁ እውነታ መድረሻው ደግሞ፡ “**በሰማይም ያለው፡ የእግዚአብሔር መቅደስ ተከፈተ! የኪዳኑም ታቦት፡ በመቅደሱ ታየ!**” በሚለው፡ በዮሓንስ ራእይ ተረጋግጦ እንደተነገረው፡ በሙሴ አማካይነት፡ ለእሥራኤል ተሰጥታ ቆይታ፡ ወደኢትዮጵያውያን ተዛውራና በአደራ ተጠብቃ የኖረችው ታቦተ ጽዮን፡ በኢየሱስ ክርስቶስና በድንግል ማርያም ሕያው ሰውነት፡ ወደሰማያት ተመልሳ በምትገኝበት ህልውናዋ የተገለጠው፡ ሌላው፡ ዕፁብ ድንቅ ተአምር ነው፡፡ (ሉቃ. ፩፥ ፴-፴፰፡፡ ዮሓ. ፩፥ ፲፬፡፡ ራእ. ፲፩፥ ፲፱፤ ፲፪፡፡)

ይህ ታላቅ ትንግርታዊ ቍም ነገር፡ እንዲህ በሚል ጥቂት ቃል፡ ሊጠቃለል ይቻላል፤ ይኸውም፡- በቅድሚያ፡ በመንፈስ ቅዱስ ምሥጢርና ጥበብ፡ በድንግል ማርያም ማሕፀን ላይ ዐርፎ የተፀነሰው፡ ያው፡ በጽላቷ ላይ ተቀርጾ የነበረው፡ የእግዚአብሔር ቃል፡ እርሱም፡ ኢየሱስ ክርስቶስ መኾኑን፥

ቀጥሎ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ የኾነችው፡ ጽላተ ኪዳንና የድንግል ማርያም ምሳሌ የኾነችው፡ የጽላቷ ማደሪያ ታቦት (ሣጥን)፡ ኹለቱም፡ በምድር ላይ ከነበሩበት ግዙፍ ህልውናቸው ተሠውረው፡ በሰውነት መገለጻቸውን፥

በመጨረሻም፡ በሕይወተ ሥጋ ኖረው፥ ተልእኳቸውንም ፈጽመው፡ በአዲሱ ኪዳን የትንሣኤ አካል፡ ከሙታን ተለይተው ከተነሡ በኋላ፡ በዚያ ሕያው አካላቸው፡ ወደሰማይ ዐርገው፡ ዛሬ፡ ኢየሱስ ክርስቶስና ድንግል ማርያም፡ በሰማይና በምድር በሰፈነችው በዘለዓለማዊቷ መንግሥታቸው ነግሠውና በሰማያዊው ዙፋናቸው ላይ ተቀምጠው የሚገኙ መኾናቸው ነው።

የእመቤታችን፡ የቅድስት ድንግል ማርያም፡ የእናትነቷና የንግሥትነቷ፥ የሃይማኖትነቷና የአገርነቷም ፍቅር፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ዘንድ፡ እጅግ የጠለቀና የመጠቀ በመኾኑ፡ ቅዱሳን ሐዋርያት፡ ለአምላክ እናት፡ ለቅድስት ድንግል ማርያም፡ ባላቸው ፍቅር፡ በጾም፥ በጸሎትና በምጽዋት (በበጎ ምግባር) ተጠምደው፡ ኹለት ጊዜያት ያካኼዱትን፡ ይህን፡ የኹለት ሳምንታት ሱባኤ፡ እኒሁ፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ በዚሁ መልክ፡ ለኹለት ሳምንታት፡ በሱባኤ ተወስነው የሚፈጽሙት፡ በዚህ ምክንያት ነው። በነሐሴ ፲፮ ቀን የሚውለውን፡ የትንሣኤዋን በዓል፥ በመስከረም ፳፩ ቀን የሚውለውን፡ የዕርገት በዓሏንም፡ "ከመ ትንሣኤ ወልዳ! ከመ ዕርገተ ወልዳ!" ማለትም፡ "ትንሣኤዋ፡ እንደልጅዋ ትንሣኤ ስለኾነ፡ እንደልጇ ትንሣኤ በዓል አድርገው፥ ዕርገቷም፡ እንደልጇ ዕርገት ነውና፡ እንደልጇ ዕርገት በዓል አድርገው ያክብሩት!" ሲሉ፡ የቀደሙት ወላጆቻቸው የደነገጉትን ሥርዓት ተከትለው፡ ኹለቱንም በዓላት፡ እንደልጇ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤና ዕርገት፡ በታላቅ ሐሤትና ይባቤ፡ በፋሲካ መልክና ይዘት ያከብራሉ።

የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ በዚህ በዓላቸው ዕለትና ወራት፡ የሚሰማቸው ደስታ፡ በቃላት ሊገለጽ የማይቻለው፡ በልጇ የትንሣኤ በዓል ጊዜ የሚሰማቸውን ይመስላል። ይህ የተመስጦ ስሜታቸው ከሚገለጽባቸውና እግዚአብሔር፡ እንደቃል ኪዳኑ፡ በየልባቸው ላይ ከጻፋቸው፡ የማኅሌትና የመዝሙር በረከቶቻቸው መካከል፡ "**ንግሥተ ሰማያት ወምድር፡ ማርያም ድንግል! ተፈጸመ ትንሣኤሃ፥ ተፈጸመ ትንሣኤሃ፥ ወዕርገታ ዘልዑል!**" እያሉ የሚያቀርቡት ዝማሬ ይገኛል፤ የዚህም ትርጉም፡ "የሰማይና የምድር ንግሥት የኾነችው፡ የድንግል ማርያም ትንሣኤና ዕርገቷ፡ እንደልዑል አምላክ ልጇ ትንሣኤና ዕርገት፡ እውን ኾኖ፡ እነሆ ተፈጸመ!" የሚል ነው።

ደግሞም፡ እግዚአብሔር፡ ለሰብአዊ ፍጡሩ ዐቅዶ ያዘጋጀው የቸርነት ሥራው፡ ለመጨረሻው ዘውድ የበቃ መኾኑ፡ በእርሷ፡ በቅድስት ድንግል ማርያም የተረጋገጠበት፡ የዚህ ዕፁብ ድንቅ ተአምሩ ዜና፡ በየጊዜያቱና በየቦታው፥ በየምክንያቱም የሚነገር ከመኾኑ ጋር፡ እኒሁ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ በዚያ በዓላቸው ላይ፡ "**ትንሥኢት እሙታን፡ ማርያም ድንግል! ከመ ትንሣኤ ወልዳ ዘልዑል!**" ማለትም፡ "ድንግል ማርያም፡ ከሙታን ተለይታ ተነሣች! ይኸውም፡ ልዑል አምላክ ልጇ እንደተነሣው ትንሣኤ ነው!" የሚለውን የምሥራች ቃል፡ በሰላምታ መልክ ይለዋወጣሉ።

ይህ የደስታ መንፈስና የድግስ ዝግጅት፡ የልጇ፡ የበዓለ ትንሣኤውና ዕርገቱ ወራት፡ እስከበዓለ መንፈስ ቅዱስ፡ ለአምሳ ቀናት ተራዝሞ፡ እንደሚከበር ኹሉ፡ የእርሷም፡ የትንሣኤ በዓሏ፡ እንደፋሲካው ሥርዓት፡ እስከነሐሴ ፴ ቀን ድረስ ሳይቋረጥ እየተከበረ ይቀጥላል።

እንግዲህ፡ እኛ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ የአዲሱ ዓመት መነሻችን ከኾነው፡ መስከረም ፩ ቀን ከሚውለው፡ ከታላቁ ርእሰ ዐውደ ዓመት በዓል በፊት፡ የዓመቱ የመጨረሻ ዓቢይ በዓላችን አድርገን፡ በየዓመቱ፡ በነሓሴ ፲፮ ቀን፡ በያለንበት በምና ከብረው፡ የበዓለ ትንሣኤሃ ለማርያም ሌሊት፡ የምንፈጽመው ሥርዓተ ቅዳሴ፡ ዮሓንስ፡ በራእዩ ያየውን፡ ያን፡ የሰማዩን ሥርዓት፡ በምድርም ላይ እውን አድርገን ነው።

ያም፡ ሊቀ ካህናታችንና ንጉሠ ነገሥታችን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ምድራዊትና ሰማያዊት መቅደሱ በኾነችው፡ በቅድስት ንግሥት እናቱ፡ በድንግል ማርያም መንበርነትና ታቦትነት ቀድሶ፡ ሓዋርያትን እንዳቆረበ፥ እንዲሁ፡ እኛም፡ የእግዚአብሔር መንግሥት በኾነችው፡ ኢትዮጵያ፡ ዕለቲቱን በማዘከር፡ መንፈሳዊት በኾነችው፡ ምድራዊት መቅደሱ፡ ያንኑ ሰማያዊ ሥርዓት፡ መልሰን መፈጸማችን መኾኑን ማመን ይገባናል።

## ጾመ ጳጒሜ።

"ጳጒሜ"፡ እኛ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ ጾመ-ፍልሰታን ፈጽመን፡ በቅድስት ድንግል ማርያም ትንሣኤ ምክንያት፡ ኹለት ሳምንቶችን፡ በፋሲካ ደስታና በሓሤት መንፈስ ከሰነበትን በኋላ፡ በመስከረም ፩ ቀን የሚውለውን፡ ጥንት፡ የፍጥረተ ዓለሙ፥ የአዳምና ሔዋን፥ እንዲሁም፡ የሀገረ ኢትዮጵያ፥ ኋላም፡ የእመቤታችን ድንግል ማርያምና የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የልደታት ቀን የሚከበርበትን፡ ታላቁን ርእሰ ዐውደ ዓመት በዓላችንን፡ በልዩ "ሱባኤ" የምንቀበልባት ዋዜማችን ናት፤ ከዓመቱ ዕለታት ተውጣጥታ የተገኘችና ለአዲሱ ዓመት፡ አንቀጽነት (መግቢያ ደጃፍነት) የተመደበች ሰሞን ስለኾነች፡ እንደጾመ ገሃድ፡ ከማናቸውም ኃጢአት ነጽተንና ለእግዚአብሔር መንግሥት፡ በእውነተኛ ንስሓ በቅተን፡ ወደመጪው ዓመተ ምሕረት ለመሸጋገር እንዘጋጅባታለን።

በዚህ መልክ፡ ከጥንት ጀምሮ፡ ከሌሎቹ፡ የዓመቱ አጽዋማታችን መካከል፡ ፯ኛዪቱና የመጨረሻዪቱ ኾና፡ በአግባቡ ስትጾም ስለኖረች፡ "ጾመ ጳጒሜ"፥ ወይም፡ "የጳጒሜ ጾም" ትባላለች።

መስከረም ፩ ቀን፡ መልካም የኾነውን፡ የጥንቱንና የአኹኑን፡ አጽንተንና ይዘን፥ ክፉዉን ኹሉ ግን፡ ካረጀው ዓመት ጋር፡ ከወዲሁ ጥለንና ትተን፥ አስወግደንም፥ የእየራሳችንን ኹለንተና፡ ለመንፈስ ቅዱስ ማደሪያነት፡ በንስሓ አድሰን፥ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከድንግል ማርያም በመወለዱ፡ የተገኘውን፡ ዘለዓለማዊዉን የምሕረት ዘመን፡ እንደአዲስ ተሸላሚ፡ የክብር ልብስን የምንጐናጸፍባትና የሕይወት አክሊልን የምንቀዳጅባት፡ ቅድስት ዕለት ናት።

አዎን! ከዚህ የተነሣ፡ የጌታችንንና የእመቤታችንን የልደት በዓላት፡ እውነተኛና ተገቢ በኾነው፡ የአምልኮ መንፈስ ለማክበር፡ ነፍሳችንንና ሥጋችንን፥ መንፈሳችንንም፡ በሥጋ ወደሙ ቀድሰን፡ ሰውነታችንን፡ ለቅዱሱ ሕይወት የምናበቃባት፥ በአገርነትና በመንግሥትነት፡ የነጻነት በዓሏን፡ በዚያች ዕለት ለምናከብርላት፡ “ኢትዮጵያ” ለተባለችው፡ እናቱና እናታችንም፡ “ዕንቍጣጣሽ! (እነሆ፡ ዕንቍ ለጣትሽ!)” ብለን፡ የደስታና የምስጋና ገጸ በረከትን የምናቀርብባት፥ እርስ በርሳችንም፡ የአበባ ነዶና ጉንጉን አዘጋጅተን፡ “የምሥራች! እንኳን አሸጋገረን! እንኳን አደረሰን!” እያልን፡ መልካም ምኞታችንን የምንለዋወጥባት፡ የተመረጠች ቀን ናት።

ስለዚህ፡ ከአሮጌው ዓመት፡ ወደአዲሱ ዓመት የምንሸጋገርባት ድልድልያችን የኾነችውን፡ ይህችን ጳጕሜን፡ እኛ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ በ“ንዑስ ሱባኤ” መልክ፡ እነሆ፡ በ“ጾመ-ኢትዮጵያ” የጾም፥ የጸሎትና የምጽዋት (የበጎ ምግባር) ሥርዓት እናሳልፉታለን።

\+ \+ \+